homes victoria | VICTORIA State Government | Families, Fairness and Housing

DX 210081

Amharic | አማርኛ

**OFFICIAL**

<Title><Given Name><Family Name>
<Address 1>
<Address 2>
<SUBURB STATE POSTCODE>

የተተረጎመ ቅጂ ያስፈልግዎታል?

**QR ኮዱን ስካን ያድርጉ**

ወይም የሚከተለውን ይጎብኙ
**homes.vic.gov.au/high-rise-victoria-renter-updates**

ውድ <Title> <Surname>

በቅርብ መድረኮች ላይ ለመሳተፍ የቻሉትን የፍሌምንግተን እና የሰሜን ሜልበርን ተከራይ ማህበረሰቦች አባላት እና እኛን ላነጋገሩን እና በብዙ መልኩ አስተያየት ለሰጡን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እናመሰግናለን። ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ የእርስዎን ጥያቄዎች መስማት እና ከእርስዎ ጋር መነጋገር መቻላችን በጣም ጠቃሚ ነበር።

ከቤት ወደቤት ከሚያዘውረው ቡድናችን ጋር ቀጠሮ የያዙ ተከራዮችንም እናመሰግናለን።
አብዛኞቻችሁ አሁን ከቡድናችን ጋር ተገናኝታችኋል እናም ፍላጎቶቻችሁን እና ምርጫዎቻችሁን ማካፈል ጀምራችኋል። ቃል በገባሁት መሰረት ደግሞ፣ ወደ ሌላ ቦታ በመዛወር ሂደት ውስጥ ስላልዎት መብቶች እና አማራጮች መረጃ ለእርስዎ ለማቅረብ እየጻፍኩ ነው።

## ለተከራዮች አክብሮት፣ እንክብካቤ እና ድጋፍ

ለሁሉም ተከራዮች ያለንን ቁርጠኝነት ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ - ቡድናችን ሁል ጊዜ በአክብሮት እና በእንክብካቤ ይይዝዎታል። አላማችን ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ውሳኔዎችን ለማድረግ የሚያስፈልግዎትን መረጃ ለእርስዎ ለማቅረብ ነው።

## ለተከራዮች የተሻሉ ቤቶች

ግባችን ለተከራዮቻችን በምንችለው መጠን ምርጥ ቤቶችን ማቅረብ ነው።
አሁን ያሉን ሰማይ ጠቀስ ፎቅ አፓርታማዎች የሥራ ዘመናቸው ወደ ማብቂያው እየተቃረበ ነው። በንድፍ እና በአፓርታማዎቹ እድሜ ላይ ችግሮች እንዳሉ እናውቃለን ይህም ማለት የጥገና ሰራተኞች የሁሉንም ሰው ፍላጎት ለማሟላት እየከበዳቸው ነው። ተከራዮች ምቹ እና የግል የውጪ ቦታ እና ዘመናዊ መታጠቢያ ቤት ያላቸው ቤቶች እንዲኖሩዋቸው እንፈልጋለን። ቤተሰቦችን እና እንዲሁም አዛውንቶችን የሚያስተናግዱ ብዙ ቤቶች እንፈልጋለን።

## ጠንካራ ማህበረሰብን የመጠበቅ አስፈላጊነት

እርስዎ የገነቡትን ጠንካራ ማህበረሰብ እንዲጠብቁ ልንረዳዎ እንፈልጋለን፣ ለዚህም ነው በአቦትስፎርድ ስትሪት (መንገድ) እና በቪክቶሪያ ስትሪት አቅራቢያ ያሉ የመኖሪያ ቤት አማራጮችን እየሰጠን ያለነው።

## በቪክቶሪያ ስትሪት እና በአቦትስፎርድ ስትሪት የአዳዲስ ቤቶች ጉብኝቶች

ፍላጎት ላላቸው ሰዎች፣ በቅርብ ጊዜ የሚኖሩትን ቤቶች አይነት እና ጥራት እራስዎ ማየት እንዲችሉ እነዚህን አዳዲስ ቤቶች የማየት እድሎችን እንሰጣለን።
ስለእነዚህ አዳዲስ ቤቶች የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ፣ እባክዎን ወደ ሌላ ቦታ የመዛወር ድጋፍ ሰጪ ቡድንን ያነጋግሩ።

## ወደ ሌላ ቦታ የሚያዘውረው ቡድን ጋር ስገናኝ ምን ይሆናል?

ወደ ሌላ ቦታ ከሚያዘውረው ቡድን ጋር ያለዎት ቀጠሮ ከ30 ደቂቃ እስከ አንድ ሰአት ሊወስድ ይችላል። በቀጠሮዎ ጊዜ:-

- ጓደኛዎን ወይም ደጋፊዎን ወደ ቀጠሮው ይዘው መምጣት ይችላሉ።
- ቀጠሮውን ሲይዙ ቡድናችን አስተርጓሚ ያቀርባል።

50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001

- ቡድናችን ስለ መኖሪያ ቤት ፍላጎቶችዎ ይጠይቃል። ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦
  - → በቤትዎ ውስጥ ስንት ሰዎች ይኖራሉ።
  - → የእርስዎ እና የቤተሰብዎ ተደራሽነት ፍላጎቶች።
  - → ምን አይነት የጤና፣ ትምህርት ቤት ወይም የድጋፍ አገልግሎቶች ሊጠቀሙ ይችላሉ።
  - → እና የአካባቢዎ ባህላዊ ግንኙነቶች እንዲሁም ባለባት (የመጀመሪያ) ነዋሪዎች ሊኖራቸው የሚችል ከምድሩ (አገር) ጋር ያለዎት ማንኛውንም ግንኙነት ጨምሮ።
- ቡድናችን እርስዎን ለማወቅ እና እርስዎን በሚስማማ ፍጥነት ለመራመድ ከርስዎ ጋር ጊዜ ያሳልፋል።
- የህጻናት የትምህርት ቤት ፍላጎቶች ግምት ውስጥ ማስገባትን ጨምሮ በኑሮዎ ላይ የሚደርስ ማንኛውንም አይነት መስተጓጎል ለመቀነስ ቡድናችን ስለ መዛወሪያ ጊዜ ያነጋግርዎታል።
- ሊኖርዎት ስለሚችሉት ሌሎች ፍላጎቶች ይጠይቁ።

ቡድናችን ፍላጎቶችዎን  የሚፈረምበት ቅጽ ላይ ያሰፍረዋል ብሎም እርስዎ እንዲፈርሙ ይጠይቅዎታል።

ፊርማዎ የእርስዎን ፍላጎቶች እንደተረዳን እና መረጃዎን በትክክል እንደ መዘገብን ያረጋግጣል። በዚህ ቅጽ ላይ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ እና ይህ የተከራይ እና አከራይ ስምምነት ወይም ውል **አለመሆኑን** እና መብቶችዎን እንደማይለውጥ ማረጋገጥ እንፈልጋለን።  ቅጹ በቀላሉ እርስዎን ወክሎ የመኖሪያ ቤት ማስተላለፍ ማመልከቻ እንድናቀርብ ያስችለናል። ይህ የእርስዎ ማመልከቻ ነው፣ እና ፍላጎቶችዎ ወይም ምርጫዎችዎ ሲቀየሩ በማንኛውም ጊዜ እንዲቀየር መጠየቅ ይችላሉ።

## በቦታው (እስቴቱ) ላይ ወደ አዲስ አፓርታማ የመመለስ መብት አለኝ?

አዎ - ወደ ሌላ ቦታ መዛወር እንዳለበት አንድ ተከራይ፣ ምርጫዎ ከሆነ ወደ ቦታው የመመለስ መብት ይኖርዎታል። የእርስዎን ፍላጎት የሚያሟሉ የመኖሪያ ቤት አማራጮችን እንዲያገኙ ከቡድናችን ጋር እንዲነጋገሩ አበረታታለሁ።

## የመኖሪያ ቤት አማራጮቼ ምን ይሆናሉ?

ቡድናችን የእርስዎን የመኖሪያ ቤት ፍላጎቶች ለመረዳት ከእርስዎ ጋር ጊዜ ያሳልፋል፣ ለምሳሌ በቤተሰብዎ ውስጥ ምን ያህል ሰዎች እንዳሉ፣ እርስዎ የሚጠቀሙባቸው ትምህርት ቤቶች ወይም አገልግሎቶች፣ እና በቅርብ ለመቆየት ወይም ወደ አዲስ ቦታ ለመዛወር ፍላጎት ካለዎት። ይህ መረጃ ቡድናችን የእርስዎን ፍላጎቶች የሚያሟሉ የመኖሪያ ቤት አማራጮችን እንዲያገኝ ይረዳዋል።

## የቤት ኪራዬ ይቀየራል?

አይ - በሚዛወሩበት ጊዜ፣ ከኪስዎ የሚያወጡት የቤት ኪራይ ዋጋ አይቀየርም። ወደ ማህበረሰብ መኖሪያ ቤት ለመሄድ ከመረጡ፣ የኮመንዌልዝ ኪራይ እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ በአጠቃላይ ለቤቶች አቅራቢው እንደሚከፈል ይጠበቃል፣ ነገር ግን በአንዳንድ አጋጣሚዎች ከኪስዎ የሚያወጡትን ውጪ ሊቀንስ ይችላል።

## አሁን ያለኝን መብት እና ኪራይ አስከብራለሁ?

አዎ። አሁን ያለዎትን የቤት መብት ያስከብራሉ ብሎም ከኪስዎ የሚያወጡት የቤት ኪራይ አይቀየርም።

## በማህበረሰብ ቤቶች ውስጥ ተከራዮች ምን መብቶች እና ጥበቃዎች አሏቸው?

የማህበረሰብ ቤት ተከራዮች ከህዝብ መኖሪያ ቤት ተከራዮች ጋር ተመሳሳይ መብቶች አሏቸው እና በመኖሪያ ቤቶች ኪራይ ህግ (Residential Tenancies Act) 1997 የተጠበቁ ናቸው።

## የማህበረሰብ መኖሪያ ምንድን ነው?

የማህበረሰብ ቤት አቅራቢዎች ማህበራዊ ቤቶችን የሚያቀርቡ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ናቸው። በመንግስት ቁጥጥር ስር ናቸው፣ ስለሆነም በመኖሪያ ቤቶች ኪራይ ህግ 1997 የተቀመጡትን ጥብቅ የአፈፃፀም ደረጃዎች ያከብራሉ።

## አዲሶቹ ቤቶች የማህበረሰብ መኖሪያ ይሆናሉ?

እንደገና የሚገነባው የመጀመሪያው ቦታ በካርልተን በኢልጊን ስትሪት ነው የሚገኘው። በእነዚህ ፎቆች (ማማዎች) ላይ እቅድ ማውጣት ተጀምሯል፣ እና እንደ የህዝብ መኖሪያ ቤቶች ሆኖ ጸድቋል።

የሰሜን ሜልቦርን እና የፍሌምንግተን ፎቆች (ማማዎች) የሕዝብ ወይም የማህበረሰብ መኖሪያ ቤት ስለመሆናቸው ይፋ ውሳኔ አልተደረገም ገና በቅድመ እቅድ ደረጃ ላይ ነን እና። እዚህ ላይ መንግስት የእነዚህ ማሻሻያ ግንባታዎች አካል በመሆን 10 በመቶ ተጨማሪ ማህበራዊ መኖሪያ ቤቶችን ለመስጠት ቃል መግባቱን ልብ ሊባል ይገባል። ስለዚህ፣ ብዙ ማህበራዊ መኖሪያ ቤቶች ይኖራሉ እንጂ ከነበረው ያነሰ አይኖርም። ትክክለኛውን ነገር ስናውቅ በእነዚህ ጣቢያዎች ላይ ምን እንደሚገነባ እንነግርዎታለን።

### ወደ ማህበረሰብ ቤት ከተዛወርኩ ለውሃ ተጨማሪ ክፍያ መክፈል አለብኝ?

ወደ አቦትስፎርድ ስትሪት ወይም ቪክቶሪያ ስትሪት ለመሄድ ከመረጡ ለውሃ ተጨማሪ ክፍያ አይከፍሉም።

### ከማህበረሰቤ ጋር እንዴት መቆየት እችላለሁ?

እስካሁን ድረስ ከመድረክ እና ከሌሎች ዝግጅቶች ያገኘነው ጠንካራ መልእክቶች አንዱ ማህበረሰቡ ለብዙ ሰዎች ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ነው።

ከመኖሪያ ቡድናችን ጋር በግል በሚወያዩበት ጊዜ ለእርስዎ አስፈላጊ የሆኑትን ሰዎች፣ ቦታዎች እና አገልግሎቶች ማጋራት አለብዎት።

የባላባት (ፈርስት ኔሽን) ነዋሪዎች ከሀገር ጋር ያላቸው ግንኙነታቸው እንደ የመዛወር ሂደቱ አካል ተደርጎ ይወሰዳል።

የአቦትስፎርድ ስትሪት እና ቪክቶሪያ ስትሪት ላይ ያሉትን አዲሶቹ ቤቶችን ጨምሮ ከቦታ ወደ ቦታ የሚያዛውረው ቡድን በአካባቢዎ ቤት እንዲያገኙ ለመሞከር ከእርስዎ ጋር ይሰራል።

### እቃ የማንቀሳቀስ ወጪዎች በሆምስ ቪክቶሪያ ይሸፈናል?

አዎ - የመንቀሳቀስ ወጪዎች በሆምስ ቪክቶሪያ ይሸፈናል።

### አማራጮችዎን ግምት ውስጥ በማስገባት

አማራጮችዎን ለማጤን የተወሰነ ጊዜ እንደሚያስፈልግ እንረዳለን። ከጓደኞችዎ ወይም ከቤተሰብዎ ጋር ለመነጋገር እና ከቡድናችን ጋር እንደገና ለመነጋገር ይፈልጉ ይሆናል።

ጓደኛዎን ወይም ደጋፊዎን ወደ ማንኛውም ውይይት ለማምጣት ይችላሉ እና ከማንኛውም ውይይት በፊት አስተርጓሚ እናቀርብልዎታለን።

### ምስጢር/ግላዊነት

እንደተለመደው መረጃዎን የምንጠቀመው ወይም የምናጋራው በ2014 የግላዊነት እና የመረጃ ጥበቃ ህግ እና የጤና መዛግብት ህግ 2001 መሰረት ብቻ ነው።

### እኛ እርስዎን ለመርዳት እዚህ አለን

በየእለቱ የሚያዩዋቸው የመኖሪያ ቤት ሰራተኞች እና ከእርስዎ ጋር እየተገናኘ ያለው ከቦታ ወደ ቦታ የመዛወር ቡድን መረጃ እና ድጋፍ ለመስጠት እዚህ አሉ። እነሱ ሁል ጊዜ በአክብሮት እና በጥንቃቄ ይንከባከቡዎታል። ብዙ ልምድ ስላላቸው አማራጮችዎን እንዲያስቡ ሊረዱዎት ይችላሉ።

በተሰጡዎት ዝርዝር አድራሻዎች በመጠቀም ከቦታ ወደ ቦታ የመዛወር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ በማንኛውም ጊዜ ማነጋገር ይችላሉ። እነዚህን ዝርዝር አድራሻዎች ማግኘት ካልቻሉ፣ እባክዎ ይህ መረጃ ለመጠየቅ የአካባቢዎን የቤቶች ጽህፈት ቤት ያነጋግሩ።

ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካልዎት እንዲያገኙን አበረታታለሁ።

ለአስተያየትዎ፣ ለተሳትፎዎ እና ለትዕግስትዎ በድጋሚ እናመሰግናለን። ይህ የተወሰነ ጊዜ የሚወስድ ነው እናም ፍላጎቶቻችሁን ለማሟላት እና የምንችለውን ሁሉ ለመርዳት ከእርስዎ ጋር ለመስራት ቁርጠኞች ነን። በማንኛውም ጊዜ እና በምንችለው ቦታ እንረዳለን።

ከአክብሮት ጋር

**ሳይመን ኒውፖርት**
ዋና ስራ አስፈፃሚ
ሆምስ ቪክቶሪያ
17 / 11 / 2023